# የብርሃን ባንክ አክስዮን ማህበር
# የባለአክስዮኖች 15ኛ መደበኛ እና 6ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣367(1) እና 370 እንዲሁም በአክስዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ 9(3) እና መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12(2) መሰረት የብርሃን ባንክ አክስዮን ማህበር የባለአክስዮኖች 15ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 6ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ጀምሮ አዲስ አበባ ቦሌ በሚገኘው ሚሊኒየም አዳራሽ ይካሔዳል። ስለሆነም የተከበራችሁ ባለአክስዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙልን የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

1. የአክስዮን ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች
   - 1.1 የዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 2185 ፤ ድህረገጽ www.berhanbanksc.com
   - 1.2 የምዝገባ ቁጥር = 06/1/28428/01
   - 1.3 የተፈረመ ዋና ገንዘብ/ካፒታል/ = 3,450,894,000
   - 1.4 የተከፈለ ዋና ገንዘብ/ካፒታል/ = 3,450,894,000
2. የ15ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች
   - 2.1 አጀንዳውን ማጽደቅ፤
   - 2.2 የተከናወኑ የአክስዮን ዝውውሮችን ማጽደቅና አዳዲስ ባለአክስዮኖችን መቀበል፤
   - 2.3 የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ. የ2023/24 ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ ፤
   - 2.4 የውጭ ኦዲተር እ.ኤ.አ. የ2023/24 ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ማዳመጥ ፤
   - 2.5 ከዚህ በላይ በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
   - 2.6 የውጭ ኦዲተር መሰየምና ክፍያቸውን መወሰን
   - 2.7 በዘመኑ የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
   - 2.8 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ወርኃዊ አበልና ዓመታዊ ክፍያ መወሰን፣
   - 2.9 የጉባዔውን ቃለጉባዔ ማጽደቅ
3. የ6ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች
   - 3.1 አጀንዳውን ማጽደቅ፤
   - 3.2 የባንኩን/ማህበሩን ካፒታል ማሳደግ፤

3.3 የባንኩን/ማህበሩን የመመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻል/ መተካት/

3.4 የጉባዔውን ቃለጉባዔ ማጽደቅ ፤

4. ማሳሰቢያ

4.1 በጉባኤው ላይ ለመገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሰረት ጉባኤው ከሚካሄድበት ቀን አስቀድሞ ባሉት ቀናት ውስጥ በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት የአክስዮን አስተዳደር ክፍል በመገኘት የውክልና ፎርም/ቅጽ በመሙላት ተወካይ በመወከል ወይም፤ በስብሰባው ለመገኘትና ድምጽ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ማስረጃ ያለው ተወካይ ዋናውን እና አንድ ፎቶ ኮፒ በጉባኤው ዕለት ይዞ እንዲቀርብ በማድረግ በወኪሎቻቸው አማካይነት መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን። ሆኖም አንድ ባለአክስዮን መወከል የሚችለው አንድ ተወካይ ብቻ መሆኑን እናሳስባለን።

4.2 የአክስዮን ማህበሩ ባለአክስዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ በሚመጡበት ጊዜ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ኮፒ መያዝ አለባቸው። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውን የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክስዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ( ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን።

4.3 በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳ ከሚደረግባቸው ጉዳዮች መካከል የቀድሞውን መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ በአንድ ላይ አካቶ በያዘውና ተሻሽሎ በተዘጋጀው የረቂቅ መመስረቻ ጽሁፍ ላይ መወያየት ይገኝበታል። ስለሆነም የተዘጋጀውን ረቂቅ የመመስረቻ ጽሁፍ ከባንኩ ድረገጽ ላይ በማውረድ መመልከት ወይም አክስዮን አስተዳደር ክፍል በመቅረብ መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

**የብርሃን ባንክ አ.ማ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**

Tel +251 116 18 57 22 / +251 116 18 57 32 / +251 116 63 20 83
Fax +251 11 662 3431 Swift BERHETAA
E-mail info@berhanbanksc.com www.berhanbanksc.com
P.O.Box 387 Code 1110, Addis Ababa,Ethiopia